ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ራዲዮ
በ ሰኔ 10 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

## ከአንድ መቶ አምሳ አንድ ዐመት በኋላ
## አገራችን ወደ ዘመነ መሳፍንት እየተመለሰች ይሆን ?

ኢትዮጵያ ከዘመነ መሳፍንት ክፍፍል ወደ ተማከለ ሀገረ መንግሥት አቅጣጫ ያመራችበት አቅጣጫ ከተከሰተ፤ ይኸውና አንድ መቶ አምሳ አንድ/ 151 ዐመት ተቆጥሯል ። ከ 1860 ዓም - እስከ 2011 ዓም መሆኑ ነው፡፡ ከዚያ የመሳፍንት ክፍፍል ያላቀቃት ፤ ቋረኛው ቴዎድሮስ ነበር ። አባ ታጠቅ ካሣ !:: ለሀገር አድነት ዕንቅፋት የሚሆኑትን እያስወገዱ ጠንካራና ዴሞክራቲክ ሀገር ለመመስረት አንድ መቶ አምሳ ዐመት ቀላል ዘመን እንዳልነበር፤ ብዙ የታሪክ ጸሐፊዎች ይስማሙበታል። እውነትም ቀላል ዘመን አይደለም ። በነኝህ ዘመናት ከሞላ- ጎደል ጠንካራ ኢትዮጵያ ተገንብታ ቢሆን ኖሮ፤ ምንኛ በታደልን ነበር ! በነኝኽ ዘመናት ውስጥ የብሄሮች ጥያቄ በአግባቡ አልተመለሰም ነበርና ሁሉም የሚመኛትን ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ሀገር መመስረት ሳይቻል ቀርቷል።

አንድነቷ የተረጋገጠባት ደሞክራቲክ ሀገር መገንባት ቀርቶ፤ ዛሬ የኅልውናዋ ጥያቄ ፤ለዜጎቿ አሳሳቢ ሆኖባቸዋል ። ከሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ አንስቶ፤ እስከዛሬዋ ዕለት ድረስ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያንገበግበው፤ ድህነቱና ጉስቁልናው፤ ረሀብ-ጥማቱ ፤ ችግሩና የግል ምኞቱ ብቻ ሳይሆን ፤የሀገሩ መኖር አለመኖር ጉዳይ እንደሆነ ሁሉም ዜጋ ይስማማበታል። አሁንም እንደወትሮው የሀገሪቱ ኅልውናዋ ጥያቄ፤ የጥያቄዎች ሁሉ ጥያቄ ሆኗል !

ማነኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ቢሆን ቅድሚያ የሚሰጠው፤ የሀገሩ ኅልውና እንደሆነ ክርክር የሚያስነሳ አይደለም ። ከተገንጣዮችና አስገንጣዮች በስተቀር ! ዜጎቿ አሁንም፤ በሂደት ጥንካሬዋን እያጎለበቱ ፤ ከህልውና ስጋት ነጻ የሆነች ሀገር ማየት አልቻሉም ። ዛሬም እንደትላንቱ ፤ የልጆቿ ምኞት ፤ የልምዣት ሆኑ ቀርቷል ። በተለያዩ አጋጣሚዎች ሥልጣን የሚነጥቁ መሪዎቿም፤ የቀዩቱን ያኽል ቆይተው ወደሚሄዱበት ሲሄዱ፤ ሀገር ከድተው፤ ሕዝብ በትነው፤ ለዐደጋ አጋልጠውና ለጠላት አስረከበው ይሄዳሉ እንጅ፤ሃላፊነት የሚሰማቸው አይደሉም። ተጠያቂነት አላጋጠማቸውም። አስገዳጅ ኃይል ኖሮ ግዴታቸውን እንዲወጡ አልተገደዱም ። አምባገነኖች ስለነበሩ፤ እንኳንስ ለህግና ለሕዝብ ተገዥዎች መሆን ይቅርና ለኅሊናቸውም ቢሆን ተገዥዎች አልነበሩም ። የመንግሥት ሥልጣን የሚጨብጡት ሁሉ፤ የኅሊናቸው ተገዥዎች ባለመሆናቸው ፤ ለነገ የሀገሪቱ መፃኢ ዕድል ቀርቶ ፤ ለራሳቸውም ቢሆን ነግ -ከነገ ወድያ ምን እንደሚያጋጥማችው ከከርሳቸው አልፈው አላሰቡም። የዐፄውና የደርግ ፍፃሜ ህያው ምስክር ሆኗል ።

ኢትዮጵያ ዛሬ ፤ "በዘመናዊ" ዘመነ መሳፍንት አገዛዝ ስር ወድቃላች ቢባል ማጋነን አይሆንም። በታጠቁ ጎሰኞችና ባካባቢ ነፍጠኞች መዳፍ ውስጥ ወድቃ እየታመሰች ትገኛለች ። እነርሱ ክልል ብለው በሚጠሩት መልከዐ- ምድር ላይ የሚኖረውን ሕዝብ ፤ እንደ ግል ርስተ- ጉልታቸው በመቁጠር፤ ያሻቸውን ይፈጽሙበታል። ብሄርና ጎሳን

መሰረት ባደረገ መልክ ተደራጅተው፤ ያካባቢ ጦር አቋቁመው፤ በጦር መሳሪያ ታጅበው፤ የዘረኝነት ሥርዐት ዘርግተው ፤ የዜጎችን ኅልውና እያጠፉ ፤ ሌሎቹንም እያፈናቀሉ፤ ሀብት ንብረታቸውን ይዘርፋሉ ።

የጎሳ አገዛዝ ፤ ስለዜጎች ህይወትና ደኅንነት፤ ሀብትና ንብረት፤ ሰብዓዊ መብትና ነፃነት ግድ የለውም። በዚህ መርህ መሰረት በተሰባሰቡት መዝገበ ቃላት ውስጥ የግለሰብ ነፃነትና ሕይወት የሚባል ነገር አይገኝም። በብሄር የበላይነትና ነፃነት ላይ ስለሚያተኩሩ፤ የጅምላ ማንነትን ፤ በጅምላ ህግና ባውራ ጎዳና ፍርድ ብያኔ ቀውስን፤ ሥርዓት- አልበኝነትን ያራምዳሉ ። ከውጭ ሀገር በጦር ማሳሪያ ታጥቀው ሲመጡ በሠላም ቦሌ አይሮፕላን ማርፊያ ለተቀበላቸው ዜጋ ፤ የሰጡት ምላሽ፤ ትጥቃቸውን ሳይፈቱ ወደ ሀገሪቱ ጫካዎች በመግባት ፤ ሕዝብ በማፈናቀልና ሀብቱን በመዝረፍ ነው። ያጎረሳቸውን ሕዝብ ጣት በመንከስ አሳዝነውታል። በድለውታል። በዚህም አገዛዙ ዋና ተባባሪያቸው አጋዥቸውም እንደሆነ ዛሬ ምንም ጥርጥር የለውም ።

ዛሬ ሀገሪቱን ፤ ራሳቸውን የአካባቢ ንጉስ ያደረጉ የመንደር ሽፍቶች የሚራኮትባት ምድር አድርገዋታል። ባልተሰጣቸው ህጋዊ ሥልጣን፤ ከሕዝቡ ግብር ይሰበስባሉ። በተቆጣጠሯቸው አካባቢዎች ላይ የራሳቸውን ህግና ደንብ በግድ ጭነው እንዳፈተታቸው ያሻቸውን ይፈጽማሉ። በተደራጀ መልክ ባንኮችን ይዘርፋሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን አዲስ አበባ ተኮፍሰው የሚገኙት የአገዛዙ ባለሥልጣናትም እነዚህን ሽፍቶች ለመያዝም ሆነ ለፍርድ ለማቅረብ ቀርቶ ስለሁኔታው አይቶ እንደ አላየ ሆነው አይኔን ግምባር ያድርገው ብለው ተቀምጠዋል። ተብባሪ መሆናቸውንም በዚህም ሆነ በሌላ ዘረኛ እርምጃቸውን ሁሉ አጋልጠዋል ። ህገ-ወጥ ንግድ ፤ የጦር መሳሪያ ልውውጥና አእምሮ አደንዛዥ ዕፅ ሳይቀር ያዘዋውራሉ። ይኸ ሁሉ ሲሆን ፤ ኃላፊነት ተሰምቶት የሚከላከላቸው አካል ሊገኝ አልቻለም። ኢትዮጵያ ፤ በአሁን ወቅት በዘመነ መሳፍንት አገዛዝ ስር ነችን የሚል ስጋትና ፍራቻ ሊመጣ የሚችለውም ለዚህ ነው።

በዚህ ምክንያት፤ ጥቂት የማይባሉ የወያኔ ቅሪቶች ፤ ከኢሕአዴግ ተገፍትረው የወጡ በመምሰል ፤ መቀሌ ላይ ተመሽገው በህግ ሳይሆን በማን አለብኝነት ነፃ መንግሥት እንዳቋቋሙ ለማሳመን ይፍጨረጨራሉ። የትግራይ ህዝብ፤ ከቀሪው ወንድሙ የኢትዮጵያ ህዝብ ጎን ሆኖ በጋራ እንዳይታገል፤ በብረት መዳፍ ጨፍልቀው ይዘውታል። አዲስ አበባ ላለው አገዛዝም እንደማይታዘዙ ንቀታቸውን በተደጋጋሚ ገልጸዋል ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ወንጀል የፈጸሙትን የሕግ ተጠያቂዎች አሳልፈን አንሰጥም ብለው ደምድሟል ። መቀሌ የመሸገው የወያኔ ቅሪት ፤ ልቡ ያበጠበት ወጠጤ ከሆነ ውሎ አድሯል። የልብ ልብ የተሰማው መሆኑን ለመግለጽ፤ የግዛት መስፋፊያ መሬቶቹን ዘርፏል። ከጎንደር፤ ከወሎና ከአፋር መሬት ነጥቆ ቸክሎ ተቀምጧል። በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘረፈው ሀብትና ንብረት ፤በተገኘ ገንዘብ የጦር መሳርያዎችን እስከ አፍንጫው ታጥቆ ፤ በአጥፊና ጠፊ ሥነአ ዕምሮ ቁራኛ ተሸብቧል ።

" እያባበሉ ነው እጅ ፤ ዘርና ልጅ !" እየተባለ እንዲሸሞነሞን ይመኛል።

"የጦር መሪው እንጅ ፤ የወታደር ፈሪ የለው " እንደሚባለው፤ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሸሽቶ በመሄዱ ፤ሌላውም እንዲሁ ፈሪ የሚመስላቸው ፤ የወያኔ መሪዎች፤ አሁንም በትላንትናው ጫካቸው ድባብ ውስጥ ሆነው ራሳቸውን ይደልላሉ። የሀገሪቱ ሁኔታዎች በብዙ መልካቸው በመለወጥ ላይ እንደሚገኙ መገንዘብ ተስኗቸዋል።

የፖለቲካው መልከዐ-ምድር በማይለወጥ መልኩ፤ ወያኔና ተባባሪዎቹ ወደማይቆጣጠረው አቅጣጭ ፍጥነቱን ጠብቆ መሄዱ ግልፅ ሆኗል ። ባሁኑ ወቅት የወያኔ የበላይነት በሌላው የበላይነት እየተተካ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ህዝብ የመጣበትን አደጋ አውቆ እስከታገለ ድረስ አንድነቱን በመጠበቅ በኩል ድል ሊቀዳጅ እንደሚችል ጥርጥር ሊኖር አይችልም።

ኢትዮጵያ ሉአላዊ ሀገር ነች እስከተባለ ድረስ ፤ ባንድ ሉዓላዊ ሀገር ሊኖር የሚችለው አንድ ህጋዊ ሀገራዊ መንግሥት ብቻ መኖር ግዴታ መሆኑ ለድርድርም ይሁን ለምርጫ የሚቀርብ አይደለም ። የአዲሱ ሹም አስተዳደር ፤ እንደ መንታ እናት ተንጋልሎ ሊያጠባ እየሞከረ ነው። መንትያዎቹን እያጠባ ያለው ግን ወተት ሳይሆን ፤ መርዝ እንደሆነ ዜጎች ተገንዝበዋል መርዝና ወተትን አደባልቃ የምታጠባ እናት ደግሞ፤ ልጆቿም አያድጉላት፤ እርሷም መካን ሆና ትቀራለች። ከዚያ በኋላ የሚሆነው መገንዘብ አያስቸግርም። የጎሳ ማንነትንና አገራዊ አንድነትን አመቻችቶና አቻችሎ ለማስተናገድ የሚቻለው፤ ከረዥሙ የሀገሪቱ ዘላቂ ጥቅምና ከሕዝቦቿ ዘላዓለማዊ ሕልውና አኳያ ሊሆን ይገባል።፡ ያ እየሆነ ነው ማለት ያስቸግራል።

በሀገረ -ኢትዮጵያ ታቅፈን አንድ ላይ መኖር አለብን የሚለው ዜጋ ሁሉ የሚስማማበት አንድ መሠረታዊ ሀቅ ቢኖር ፤ የሀገሪቱ የመኖር- ያለመኖር ጉዳይ ነው። የርዕዮተ ዐለም፤ የሥርዓተ- መንግሥትና አስተዳደራዊ መዋቅር፤ ወዘተ.. የሀገርና የሕዝብና የሀገር ኅልውና ተረጋግጦ ከተመሰረተ በኋላ ይሆናል። ኢትዮጵያን አፍርሰን እንደገና በአዲስ መልክ እንፈጥራታለን የሚለው ቅዠት ፤ ቴዎድሮስና ምንሊክ ቢሰሙ፤ አጽማቸው በመቃብሩ ውስጥ የሚገለባበጥ ይመስለናል።

ሀገር ሸክላ አይደለችም፤ ወይም የምትታደስ አሮጌ ፍራሽ ። ለወቅቱም ሆነ ለተተኪው ትውልድ፤ ኢትዮጵያ ሀገሩ ፤ አልፋ-ኦሜጋ መሆኗን አጥብቆ ያምናል። የዛሬው ትውልድ፤ ይኽን የማይናጋ ዕምነቱን አስረግጦ ለመቀጠል ፤ በቆራጥ እርምጃ ለመራመድ፤ የማይበገር አቅም እንዳለው በተግባር ማሳየት ይጠበቅበታል።፡ እስከዛሬ ድረስ የባከነው አቅም ፤ በአመዛኙ፤ ለሀገር ግንባታ ሳይሆን፤ በአፍራሽነት ላይ ነበር ቢባል ከዕውነት የራቀ አይደለም።

በተለይ ባለፉት ተከታታይ ዘመናት የተመዘገቡት ድርጊቶች ሁሉ ጥፋትን፤ እርስ በእርስ ግድያን ፤ እስራትን ስደትንና መከራን ብቻ ነበር። ምናልባትም፤ ደፍረን ዕውነቱን ማፍረጥረጥ ካለብን፤ በእነዚህ ዐመታት ፤ ዲያቢሎስ ብቻ ሊሰራው የሚቸውን ሁሉ አስቃቂና ዘግናኝ ድርጊት በኢትዮጵያውያን ላይ መፈፀሙ አሌ የሚባል አይደለም። ዛሬ መጥፎ ድርጊቶች የሚባሉት ሁሉ ተፈጽመው አብቅተዋል። የቀረው መልካም ሥራ ባቻ ሆኗል። መልካም መልካሙን ብቻ መሥራት አለብን ብለን መነሳት ካለብን፤ በተግባር እንድናሳይ ይጠበቅብናል ። ይኽንን ተግባር ከጀመርን ፤ የሀገሪቱን ትንሣዔ ማብሰር እንችለለን። ወደ ገሀነመ-ዕሳት የሚወስደውን ጨለማ ጎዳና እያዘጋን፤ የተስፋ ጭላንጭል የሚፈነጥቅበትን የብርሃን አድማስ ርምጃ ማፋጠን አያስቸግረንም ።

ሌላው በቀደደው ቦይ ከምንሳፈፍ፤ በራሳችን ባህረ-ኃሳብ አውራ መንገድ ተማምነን መሄድን እናስቀድማለን። ድሪቶን ከመደረት ወጥተን፤ አስልችና አንገፍጋፊ ፤ ተደራራቢና ተደጋጋሚ ከሆነ ክስተትና ድርጊት ተላቅቀን ወቅታዊና ነባራዊ በሆኑ ተግባራት ካተኮርን፤ ውጤት አስመዝጋቢ መሆን እንችላለን። እስካሁን የተከሄደው መንገድ ፤ ከአትራፊነቱ ይልቅ አከሳሪነቱ ያጋድላል ። ከእንግዲኽ ወዲህ በአትራፊ ተግባራት ላይ ካላተኮርን፤ ዘመንና ትውልድ አልፈውን መሄዳቸን ይቀጥላሉ። አኩሪ ታሪክ አስመዝግበው ያለፉት፤ የዚያ ጀግና ትውልድ አባላት፤ ቅድሚያ የሰጡት ፤ በታሪክ

ገጽ ምን ቦታ እናገኝበታለን ? ብለው ሳይሆን፤ ሕዝባችውን ከመከራ ሀገራቸውን ከጥፋት ለመታደግ ብቻ ሲሉ ነበር። ጥረቱ አሁንም ቀጥሏል ። የእልህ ሳይሆን ፤ የዓላማ ጉዳይ ነውና ዓላማው ግቡ እስኪመታ መቀጠሉ አይቀርም። ለመቀጠል ግን፤ አዲሱን ትውልድ ታሳቢ ባደረገ አመለካከት ሊሆን ይገባል ።

ዓላማን ከግቡ አድርሶ፤ አትራፊ ውጤት ማስመዝገብ የሚቻለው፤ በተጭባጭ እውነታ ላይ ሲያተኩሩ ብቻ ይሆናል። እውነታው የሚያሳየው፤ ሀገሪቱ ዛሬ በዘመነ-መሳፍንት ዓይነት ሁከትና አለመረጋጋት ስር የገባች መምሰሏ ነው። ጠባብነትና ኢትዮጵያዊነት ግብ ግብ ገጥመዋል። ነዋሪዎቿ ነፍጥ ባነገቡ ልዩ ልዩ ድርጅቶች ስር ወድቀዋል። ሽፍቶቹና አገዛዙ አንድ ናቸው፤ ጠባብ ዘረኞች ። ሠላምና ደኅንነት አልተረጋገጡም ። በጤና ወጥቶ መግባት ዋስትና አላገኘም። በመሪዎች ተብዬዎችና በዜጎች መካከል መተማመን መጥፋት ብቻ ሳይሆን የጠላትነት ፍረጃ ዋናው ሆኗል ። አለማወቃቸውን የማያውቁ ስፍር-ቁጥር የሌላቸው ቲያትረኞች ሕዝብ ማወናበዳቸውን በሰፊው ቀጥለውበታል። ኢትዮጵያን ያኽል አገር ማስተዳደር፤ እንደ ኳስ ሜዳ ጫጫታና ጩኸት ቀላል የሚመስላቸው ቡድኖች የወቅቱን ግርግር ፤ለየግል ፍላጎታቸው ማራመጃ ለማድረግ ላይ ታች ሲሉ ይታያሉ ። " ካልተበጠበጠ አይጠራም " ባዮች፤ ሕዝብ ማበጣበጣቸውን በሰፊው ቀጥለውበታል። ከተሞችና አውራ ጎዳና መንገዶች የቅሚያና የዝርፊያ መናህሪያዎች ሆነዋል። የሥራ አጦችና የጎዳና ተዳዳሪዎች፤ ቁጥር በየጊዜው እያጨመረ በመሄድ ላይ ነው። ሥርዓተ-አልበኝነትና የቡድን ወንጀሎ በርክተዋል፤ተስፋፍተዋል ።፡ የሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ሁኔታ " ተከድኖ ይብሰል " ከሚባልበት ደርጃ ላይ ነው። የውጭ ምንዛሬው እፍ ሲሉት ጭልጥ ሆኗል።ከብድር የሚመጣው ዕዳ፤ የዛሬውን ትውልድ ብቻ ሳይሆን ፤ የሚመጣውንም ትውልድ ጭምር፤ ያልበላውን ዕዳ ከፋይ አድርጎታል ። ትውልዱ ሁሉ በወለድ -አገድ ( ሞርጌጅ ) ታስሯል። በሀገሪቱ ስም የተበደሩት ባለሥልጣናት ግን የተበደሩትን ዘርፈው ሄደዋል። ሚሊዮኖች በረሃብ ይጠበሳሉ። ይኽ ክስተት፤ የሀገሪቱ ተፈራራቂ ዕድሎች መገለጫ ሆኖ ቀርቷል። ይህ ሁሉ ግልጽ ያለ ሀቅ ሆኖ ሳለ እጅ እጅ ባለ ቅጥፈታቸው ፤ የሀገሪቷ ኤኮኖሚ በዘጠኝ በመቶ ሊያድግ አቀብቁቧል ይሉናል ። ሰው በጠፋበት ሀገር፤ ሰው ፈልጎ ማግኘት አልተቻለም። ያልፈጠሩትን ሰው ለመፈለግ መሞከር ፤ ላም ባልዋለበት ኩበት መልቀም እንደመሞከር ነው። ሰው ከሌላ ሰው አይገኝም። ሰው እንዲወጣ ያላደረገ ኅብረተስብ ፤ የሀገር መሪዎች፤ ሕዝባዊ ዐርበኛ፤ ዐዋቂና ምሁር፤ የሀገር ሽማግሌና መካሪ አያገኝም ። የዚኽ ሁሉ ድምር ውጤት ፤ " ዕውራን ዕውራንን ከመሩ፤ ተያይዘው ተደናበሩ " ሆኖ ይቀራል።

ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ ከጠባብ የጥላቻ አመለካከትን አሽንፎና አስወግዶ፤ የሀገሪቱንም ሆነ የራሱ መፃኢ ዕድል ወደ ተሻለ ምዕራፍ ለማሸጋገር ብልሃት መፈለግ አለበት ! መጀመሪያ ግን፤ ከውያኔ ኢሕአዴግ አገዛዝ ነፃ ሊወጣ ይገባል ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር !